Association of Ethiopians in Europe
info@ethiodiaspora.net www.ethiodiaspora.net

ቀን: 09.10.2020 (እንደ አውሮፓ አቆጣጠር )

ከኢትዮጵያውያን ማህበር በአውሮፓ
ፍራንክፉርት ጀርመን

ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠ/ሚ ክቡር ዶክተር አብይ አሕመድ፤

ክቡር ጠቅላይ ሚንስትር፤ ክቡራን የምክር ቤቱ አባላት

ጉዳዩ፥ **በሥራ ላይ ያለውን ሕገ መንግሥትና የምርጫ ጊዜ ሰሌዳን ይመለከታል፤**

እኛ የሀገራችን የኢትዮጵያ ጉዳይ ግድ የሚለን፣ በተለያዩ የአውሮፓ ሀገራት ነዋሪ የሆንን ኢትዮጵያውያን 'በአውሮፓ የኢትዮጵያውያን ማሕበር" በሚል ሕጋዊ እውቅና ባለው ጥላ ስር ተሰባስበናል። አባሎቻችን በየምንኖርባቸው ሀገራት በተለያዩ ዘርፎች ለኢትዮጵያ ልዩ ልዩ አስተዋጽዖ ያደርጋሉ። የሀገራችንን ጉዳይ በንቃት እየተከታተልን የምንኖርባቸው ሀገራት የውጪ ግንኙነት ተጠሪዎች ሙሉ መረጃው እንዲኖራቸው በማድረግም ላይ እንገኛለን። እንደ ማሕበር ሥራ ከጀመርንበት ካለፈው ሚያዝያ ወር ጀምሮ ጠንካራ የዲፕሎማሲና የመረጃ ልውውጦች በተሳካ ሁኔታ አከናውነናል። የአባይ የመጀመርያው ዙር ሙሌት በአውሮፓ መገናኛ ብዙሃን ግብጾች በፈለጉት መጠን እንዳይራገብ፣ የተዘገበውም እኛን በመደገፍ መሆኑ አንዱ ማስረጃ ነው።

እንደሚታወቀው ለዘንድሮ መስከረም ወር ታቅዶ የነበረው 6 ተኛው የሕዝብ ተወካዮችና የጠቅላይ ሚንስትር ምርጫ በልዩ ልዩ አስቸጋሪ ምክንያቶች ቀደም ብሎ በወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ሊካሄድ አልቻለም። አንድ አንድ አካላት በታቀደው ቀንና ሰዓት ምርጫ ስላልተደረገ አሁን ያለው መንግሥትም ሆነ የተወካዮች ምክር ቤት አባላት ከመስከረም 30 ቀን በኋላ ሕጋዊ አይደሉም ሲሉ ይደመጣሉ። ለዚህም ሀገሪቱ ላለችበት የሰላም መደፍረስና ፍጅት በዋናነት ተጠያቂ ሊሆን የሚገባው ጸረ ኢትዮጵያ/ጸረ አንድነት ኃይሎች የሸረቡትና ወደማያባራ የባሰ ፍጅት የሚመራ 'ሕገ መንግሥት የሚሉትን ሰነድ በመጥቀስ ነው።

በመግቢያችን ላይ እንደገለጽነው፣ እኛ በአውሮፓ አህጉር የምንኖር ኢትዮጵያውያን ከምንኖርባቸው ሀገራት ከቀሰምናቸው መጠነ ሰፊ የትምሕርት፣ ሥራና የሕይወት ተመክሮ በመነሳት አሁን የኢትዮጵያ መንግሥት የሚተዳደርበትን ሕገ መንግሥት ስንመረምር የሚከተሉትን ጉልህ ግድፈቶች አግኝተናል።

ሀ. በዓለም ላይ ካሉ 195 ሀገራት ሁሉ በተለየ ሁኔታ የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት የግለ ሰብን መብት በሚደፈጥጥ መልኩ የሚጀምረው ትርጉም አልባ በሆነ "እኛ ብሔር ብሔረ ሰብ" በሚል የወል መጠርያ መሆኑ፥

ለ. በተባበሩት መንግሥታት ድርጅትም ሆነ ሌሎች የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ለምሳሌ እንደ Human Rights Watch ን በመሳሰሉት ይኸንን ሕገ መንግሥት " ግልጽነት የጎደለው"(Vague) ተብሎ መጠቀሱ፥

ሐ. አዲሲቷ ኢትዮጵያ"ን እንፈጥራለን በሚል ፈሊጥ ታሪካዊቷንና የአፍሪቃ የነፃነት ተምሳሌት፣ የጥቁር ሕዝቦች ኩራት የሆነችው ኢትዮጵያ ሀገራችንን ለማፈራረስ የተሸረበ ሴራ መሆኑን እንረዳለን። ይልቁንም  አሁን ያለው ሕገ መንግሥት ጸረ_ኢትዮጵያ የሆኑ ግለሰቦች ተቧድነው የወሻሸሉት እንጂ እኛ የምናውቃትን ከሦስት ሽህ ዓመታት በላይ የተመዘገበ ታሪክ ያላት ኢትዮጵያን የሚወክል ስላልሆነ ሰነዱ በአብዛኛው መለወጥ እንደሚገባው ተማምነንበታል።

ስለዚህ እነዚህንና ሌሎች መሰረታዊ ግድፈቶችን በማግኘታችን፣

የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት፣ የተከበሩ ጠቅላይ ሚንስትር አብይ፤ ይህን የታሪክ አጋጣሚ ተጠቅማችሁ የተበላሸውን ለማሻሻል የተጣመመውን ለማቃናት ትጠቀሙበታላችሁ ብለን አሁን መንግሥት የሚጠቀምበትን ሕገ መንግሥት በከፊልም ቢሆን ሊተካ ይችላል ብለን፣ ከላይ የተዘረዘሩትን ግድፈቶች የሚቀርፍ የ"ሕገ ኢትዮጵያ"ን ረቂቅ አሰናድተን ከዚህ ደብዳቤ ጋር ልከናል።

ከላይ ከተዘረዘሩት እንከኖች በተጨማሪ አሁን በሥራ ላይ ያለው ሰነድ("ሕገ መንግሥት") የኢትዮጵያን ሕዝብ የዜግነት መብት የገፈፈ፣ ሰዎችን በሀገራቸው ባይተዋር ያደረገ ከመሆኑም በላይ መሰረታዊ የሆኑ የዲሞክራሲን የመምረጥና የመመረጥ መብት ያላገናዘበ እንደሆነ ግልጽ ነው። ስለሆነም 21 ኛውን ክፍለ ዘመን የሚመጥን ሕገ መንግሥት ለሀገራችን ለኢትዮጵያ

ከማዘጋጀት ጀምሮ በሚከተሉት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ የተሻሻለ ሕገ መንግሥት የሚቀጥለው 6 ተኛ ሀገራዊ ምርጫ ከመደረጉ በፊት ለሕዝብ ውይይት አቅርቦ እንዲያስጸድቅ፣ አሁን የሥራ ጊዜውን ያራዘመው መንግሥትና የተወካዮች ምክር ቤት ሃላፊነቱን እንዲወስድ በድጋሚ እናሳስባለን።

እኛም በቅርቡ በምንልከው ረቂቅ ሰነድ ውስጥ ሁሉም የተዘረዘረ ቢሆንም በሚከተሉት ዐበይት ነጥቦች ላይ አጽንዖት እንዲደረግባቸው በድጋሚ እንጠቅሳቸዋለን።

- ሕገ መንግሥቱ በጎሣ ላይ የተመሰረተ ፌደራሊዝምን ሙሉ በሙሉ እንዲቀይር
- ክልል የሚሉት ሕዝብን ከሕዝብ ነጣጥሎ የሚያራርቅ ማነቆ ለአስተዳደር በሚመች መልክአ ምድራዊ አቀማመጥን በተመረኮዘ ክፍለ ሀገራት እንዲተካ፤
- በየክልሉ የሚኖሩ የክልሉ ተወላጅ ያልሆኑትን የዜግነትና ሰብአዊ መብትን የሚያስጠብቅ እንዲሆን፣ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የትም ይኑር የት ወይም የትኛውም ቋንቋ ተናጋሪ ቢሆን በመረጠው የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገራት የመኖር፣ የመምረጥም ሆነ የመምረጥ መብቱ ሙሉ በሙሉ እንዲከበር፤
- በውጪ ሀገራት ነዋሪ የሆኑ/ የተወለዱ ኢትዮጵያውያን ካለ ምንም ገደብ የዜግነት መብታቸውን / ኢትዮጵያዊነታቸውን እንዲያስጠበቅ፥ የሌላም ሀገር ዜግነት ያላቸው ኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያዊነታቸው እንዲከበር (dual Nationality) እንዲፈቀድ፣
- የውሸት ትርክትን ተመርኩዞ የተዘራው ሕዝብን ከሕዝብ የሚያፋጅ የፈጠራ ታሪክ በሕግ ታግዶ በእውነት ላይ በተመሠረተ እንዲተካ፤ የትምሕርት ካሪኩለም/አሰጣጥ እንዲስተካከል፥
- የሀገሪቱ / የመንግሥቱ ስርአተ መርህ በፕሬዝዳንት ሆኖ ሕዝብ በቀጥታ መሪውን እንዲመርጥ።

ቢደረግ ሀገራችን ከተደቀነባት የመፈራረስ አደጋ ትድናለች ብለን በፅኑ እናምናለን።

ኢትዮጵያ ታፍራና ተከብራ ለዘለዓለም ትኑር!

የኢትዮጵያውያን ማሕበር በአውሮፓ፣ ፍራንክፈርት/ጀርመን

መስከረም 28 ቀን 2013 ዓ.ም.

ግልባጭ፥ ለክብርት ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴ

ለክቡር የፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ

ለኢትዮጵያውያን የመገናኛ ብዙሀን በሙሉ